# የእኔ ዘመን ትውልድ

በዳግማዊ ሲሳይ

በቅኝ ያልትገዛች ሀገር ላይ ተወልዶ ላደገ፣በነፃነት ተከባ ታፍራና ተከብራ በኖረች ሀገር ላይ ተወልዶ ላደገ፣ የወንዞቿ ኽረት፣ የጋራ ሽንተረሯ ልምላሜ እና አረንጓዴነት መስብነቱ በአለም ብቸኛ እንደሆነች እየተነገረው፣ እየተዘፈነለት፣ እየተገጠመለት፣ ላደገ የእኔ ዘመን ትውልድ፤

ከ፹ በላይ ብሄር ብሄረሰብ ያለባት ሀገር፣ የበርካታ ቋንቋዎችና የቱባ ባህል ስብስብ የሆነች የተለየች ምድራዊ ገነት ውስጥ እንደተወለደ ሲነገረው ለኖረ፣አያት ቅድመ አያቱ አባትና እናቱ፣ ምንዥላትና ቅድመ ምንዥላቱ፣ በገበሩት ዕድሜ፣ በቆረሱት ስጋ፣ ባፈሰሱት ደም፣ በከሰከሱት አጥንት፣ ዳር ድንበሯ ተከብሮ፣ ትንሽም ተቆርሶ፣ አንገቷ ተቀንጥሶ ባቆዩለት ሀገር እየኖረ ላለው ለእኔ ዘመን ትውልድ

አግኝቶ ማጣቱ የማያስቆጨው፣ የባሰ አታምጣ ብሎ ስንፍናውን በአምላኩ ላይ ላላከከ፣በሶስት ሺ ዘመን ስልጣኔ በአክሱምና ላሊበላ ሃውልት ዘመን አይሽሬነት ተኮፍሶ እየኖረ ላለው ለእኔ ዘመን ትውልድ

መነጋገር፣ መወያየትና የመረጠውን የፖለቲካ አቋም መያዝ እንደነውር ለሚቆጥር ወይም እየቆጠረ ላለ፣የሞራል ህልውናው አደጋ ላይ ወድቆ በዘመናዊነት ስም ራሱን የሚሸውድ፣ፀጉሩን ማንጨብረር፣ ሱሪውን ዝቅ ማድረግና በምዕራባውያን ሙዚቃ ያበደ፣በዘርና ጎሳ፣በፆታና ሀይማኖት የጎሪጥ የሚተያይ፣ ምልክታው የተንሸዋረረ የእኔ ዘመን ትውልድ

ህዝብ በመንግስት፣ መንግስት በህዝብ ላይ ያቄመና ለበቀል የሚፈላለግ ወይም በቀሉን የተወጣ፣ዕልህ መጋባትና ትዕግስት ማጣት የነገሰበት፣ በመማሩና መመራመሩ ሀገሩን ለማሳደግ ከችግር ነፃ ለማውጣት ከመታተር ይልቅ አይኑን ወደ ውጭ ያነጣጠረ አነጣጥሮም ያልቀረ የኮበለለ፤የተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች ፎቶ እየተነሳ የሚለጥፈው ኩሩውና ደልቃቃው የእኔው ዘመን ትውልድ

የሀገሩ አባዜ የማይለቀው፣ ከተሰደደባቸው ሀገራት ህዝቦች ጋር አብሮ ለመኖር የተሳነው፣ ከሚያገኘው ገቢ ላይ ቤተሰቡን ለመደገፍ የሚውተረተረው ትንሽም የሚሰስተው ወይም የማይበቃው፣ ሰክኖ የተሻለ ሃሳብ ከማፍለቅ ይልቅ አፉን በስድብ እሾህ ያጠረና መግባባት የተሳነው፣ መፅሐፍ ከአነበበ አመታት የተቆጠሩበት ግን ደግሞ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥዶ

የሚውል (ላይክ)))በመጠቅጠቅ የተጠመደ፣የፌስ ቡክ ነጠላ ሴቶችን እያደነ በሰላምታ ጋጋታ የሚያስጨንቅ፣የሚጀነጅን፣የሚጎንትልና የሚያመነዝር የዋሁ የእኔ ዘመን ትውልድ፤

ነውር የነገሰበት፣ ታናሽ ከታላቁ ለመማር ፍላጎቱ የጠፋበት፣ አላዋቂነት የነገሰበት እና ድንቁርና የዘመነበት፣ ማወቅ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያስከብር ሳይሆን ዋጋው የወረደበት ወይም ዋጋ የሌለው ወይም ዋጋ የማያወጣበት፤ድርጊቶችን ከመፈፀም በፊት ዕውቀትና አሃዞችን በተገቢው መንገድ አቀናብሮ ተንትኖና አስተሳስሮ አጣፍጦ በአሳማኝ መንገድ የሚያቀርብ የጠፋበት፤በአንድ ጀምበር በግንጠላ፣ በበልተን እንብላ መርህ ቱጃር የሚኮንበት (ምቅኝነት አይደለም)፣ግራ ግብት ያለበት ዘመን፣ ታሞ ለሚያጣጥር መርዳትና ማሳከም ሲገባ ሲሞት አበባ ለማስቀመጥ ሩጫው የቀለጠበት፣ ስንወለድ በገንፎ ስንሞት በንፍሮ የምንሸኝበት፣ በአንድ ሀገር በአንድ ከተማ ውስጥ ጉራማይሌ ኑሮ የሚኖሩበት ይህ የእኔ ዘመን ትውልድ

ተርቦ ጎዳና ላይ ወድቆ አይዞህ ባይ ያጣው፣ በሃመር መኪና ተቀልሎ እየገረመመ በደሃው እያላገጠ የሚሄደው፤በኪራይ ሰብሳቢነት የበሰበሰ አይን የበላ፣ ኪራይ አሰብሳቢው ከጭንቅላቱ ጀምሮ የበሰበሰበው፣ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ የተጠመቀው፣በቀኝና ግራ ዘመም ፖለቲካ ባህር ውስጥ ገብቶ የሚዳክረው፣ እንደ በቀቀን የተነገረውን ከጠዋት እስከ ማታ አለመታከት የሚደጋግመው የእኔ ዘመን ትውልድ

ጭፍን ደጋፊውና ጭፍን ጠይው፣ ምህዳሩ ቢሰፋለትም ቢጠብለትም ከተስፈኝነት ወደ ጨለምተኝነት የሚያዘግመው፣ በነፈሰበት የሚነፍሰው የአርችና ማንቼ ጉዳይ እንቅልፍ የሚነሳው፣ ጎራ ለይቶ ቡድን መስርቶ የሚቆራቆሰው፣ ድንጋይ የሚወራወረው፣ በአንድ ሃይማኖት ሁለት ጳጳስ (የተቃዋሚና የደጋፊ)፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ያለው (ሁለት እግዚአብሄር ያለ ይመስል)የአልኮል ወገብ ይዞ የሴትን መቀመጫ ተንተርሶ ከምሽት እስከ ንጋት በየምሽት ክበቡ የሚያመሸውና የሚያድረው፣ከምሽት የስጋ ገበያ (ሽንጥና ዳሌ፣ወገብና ደልዳሌ)የሚያማርጠው፣ምሽትና ልጁን ቤቱ አስተኝቶ ውስኪ ብርጭቆ ስር የሚደበቀው የእኔ ትውልድ

ስርጉን ተበድሮ ደግሶ በመልሱ ጥሪ ዕለት ለፍቺ ፍርድ ቤት በራፍ ላይ ተራ የሚጠብቀው፣ማክዶናልዱን ገምጦ ኮካውን አንደቅድቆ በፌስቡክ ሪሞት የሀገሩን የተቃውሞ ትግል የሚመራው የእኔ ትውልድ

እናት ሀገሩን በጦር ለማስወጋት፣በቦንብ ለመደብደብ ገንዘብ የሚያዋጣው፣ገዢው ፓርቲ ይውረድ ብሎ ክዲሲና ብራስልስ ደጃፍ የማይጠፋው፣ ለጥገኝነት በሔደበት ሀገር የውሸት አሳማኝ ኬዝ እየሰራ የሚኖረው (ኑሮውን ለማሻሻል)፣ጉዱንና ገመናውን የማይደባበቀው፣ጥገኝነት ለሰጠበት ሀገር ባለስልጣናት እየሔደ የሚያጋልጠው

(የሚያቃጥረው) የእኔ ትውልድ

ቤቱ ቁጭ ብሎ እየበላ በጀርባው ሄዶ የሚበላው (የሚወጋው)፣ለመኖር የሚበላ ሳይሆን ለመብላት የሚኖረው፣በሙዚቃ (ግጥምና ዜማ)ስርቆሽ ዝነኛ የሆነው፣በኩረጃ ከፍታ ላይ ወጥቶ አቆልቁሎ አስኮራጁን የሚደቁሰው፣ለቅዳሴና ለሶላት ስግደት ቤተክርስቲያንና መስጂድ በራፍ ላይ የማይጠፋው፣ከዛ መልስ ጥንቆላ ቤቶችን የሚያጨናንቀው፣ምርቃትና ርግማን በጣም የሚያስፈራው ለርግማን ግን የሚቅድመው የሌለው፣የሃሳብ ባህር ውስጥ የሚዳክረው፣ከውቂያኖስ ሀጢያት ውስጥ የቻልውን ያህል የጠለቀው የእኔ ትውልድ

በኦባማ መመረጥ ዲሲ ስትፈነጥዝ አዲስ አበባ ላይ የሚያስነጥሰው፣በማይክል ጃክሰን ሞት መሃል አራዳ ላይ ድንኳን ጥሎ ሀዘን የተቀመጠው፣አርባና ሰማንያውን ተዝካር ያበላው (ትንሽ ሳጋንነው)አብሮ መብላት ባህሉ መስራት ግን ጥሉ፣ጥንካሬ አልባው ልፍስፍሱ፣ለህልሙ መሳካት ከመጋፈጥ ይልቅ የሜድትራኒያን ባህርን የደፈረው ልፍስፍሱ፣ከነዱ አይቀር መርሰዲስ ከሞቱ አይቀር በኤድስ የሚል መፈክር በአንድ ወቅት በሰፊው ያስተጋባው  የእኔ ትውልድ

በማንነት ቀውስ ውስጥ እየዳከረ ቋንቋውን የበረዘ፣የቀየጠ፣የደቀለ፣ያዳቀለ፣ኢዝና ወዝን ስለለየ ወዘናው ከሩቅ የሚያበራው፣በቅኔ ህብረ ቃል፣ሰምና ወርቅ የሚደናበረው፣ውሉ የጠፋው ወይም የሚጠፋው ወይም የሚያጣፋው ይህ የእኔ ትውልድ

ካለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ የፎከረው ፎክሮም ያልቀረው፣ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ክምስራቅ እስከ ምዕራብ በደም የታጠበው፣ህዝብን ካገለገለ ወይም በህዝብ ከተገለገለ በሗላ ስልጣኑን በሰላም ለተተኪው ከማስረከብ ይልቅ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው ብሎ ከስልጣኑም ከዛፉም ሳይሆን ወድቆ ለተከሰከሰው፣ጥርሱን ለለቀመው፣እግርና እጁን ለሰበረው፣ወገቡ እንክትክት ላለው፣በቃኝን የማያውቀውና እስትንፋሱን ለማስረዝም እየታደሰ፣በጥልቅ እየታደሰ ቀሪ ፪፯ አመት ለመግዛት የሚቋምጠው የእኔው ብልጡ ብልጬ ነቂው ትውልድ

ዶላርን (ደላር)፣ዩሮን (ኤውሮ)፣ፓውንድን (ፖንድ)ብሎ የሚጠራውና ለመጥራት የማያፍረው፣ወርቅን በባሌስትራ ለውጦ ታሪክ የሰራው፤ጀሶን ከጤፍ፣በርበሬን ከሸክላ፣ነጭ ጋዝን ከሽንት ጋር ቀላቅሎ የሚሸጠው፣ግልገል ጊቤ ፩ ፪ ፫ የሀይል ማመንጫ የሰራው፤ በተመረቀበት ዕለት ግን በሻማ ያደረው፣ ሳይወድ በግድ በየቀኑ ካንድል ዲነር የሚበላው፤ንፁህ መጠጥ ውሃ አጥቶ በየቀኑ ባለ ፳ ሊትር ጀሪካን አንዷ በጀርባው፣ሁለቱ በአህያ ጀርባ፣ሶስቱ በባጃጅ ጀርባና ወዘተረፈ የሚያጋግዘው፤በለጬና ቁጦ፤ገለምሶና አወዳይ እየቀነጠበ በምርቃና ላበደው ለእኔው ምስኪኑ ትውልድ::